የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

**February 12, 2026**
Ethiopian Capital Market Authority
Addis Ababa, Ethiopia

# ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY (ECMA) GRANTS LICENSE TO BDO CONSULTING PLC.

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) has granted a Capital Market Service Provider (CMSP) license to BDO Consulting PLC, authorizing the company to operate under the Securities Investment Advisor(corporate) category. In addition, the ECMA has approved the licensing of three (3) Appointed Representatives and approved the appointment of five (5) board directors within BDO Consulting PLC.

The license was officially issued on Thursday, February 12, 2026, raising the total number of licensed CMSPs in the country to sixteen (16) and total number of Securities Investment Advisors to nine (9).

The Director General of the ECMA, Hana Tehelku, formally presented the license to the leadership of BDO Consulting PLC.During the license ceremony, she emphasized the critical role of securities investment advisors in the development of the capital market and investor protection by equipping investors to make an informed decision. Furthermore, the Director General urgeslicensed capital market service providers to prioritize investor interests, maintain transparency, and ensure compliance with capital market regulatory frameworks.

The Ethiopian Capital Market Authority congratulates BDO Consulting PLC and reiterates its unwavering commitment to fostering a strong, inclusive, and resilient capital market that supports sustainable economic growth and investor protection in Ethiopia.

---

**For enquiries & additional information contact**

**Contact:** Communications & Public Relations Directorate
**Phone:** 011-5-57-81-62
**Email:** communication@ecma.gov.et

የካቲት 05፣ 2018 ዓ.ም
የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለ ቢ ዲ ኦ ኮንሰልቲንግኃላ/የተ/የግ/ማህበር ፈቃድ ሰጠ።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያባለስልጣን ለ ቢ ዲ ኦ ኮንሰልቲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የካፒታልገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ሰጥቷል። በዚህም ድርጅቱበድርጅት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪነት ዘርፍእንዲሠራ ፈቃድ ተሰጥቶቷል።

በተጨማሪም ባለስልጣኑ ለ ቢ ዲ ኦ ኮንሰልቲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ሦስት (3) ተሿሚእንደራሴዎችም ፈቃድ የሰጠ ሲሆን የአምስት (5) የቦርድ አባላትሹመትንም አጽድቋል። የአገልግሎት ሰጪነት ፍቃዱም በዛሬው እለት ሀሙስ የካቲት 05፣2018 ዓ .ም በይፋ የተሰጠ ሲሆን ይህም በአገሪቱ ውስጥ ያሉትንየተፈቀደላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ጠቅላላቁጥር ወደ አስራ ስድስት (16)፣ እንዲሁም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎችን ቁጥር ወደ ዘጠኝ (9) ከፍአድርጎታል።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሃና ተኸልቁ ፈቃዱን በይፋ ለቢ ዲኦ ኮንሰልቲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር አመራር አስረክበዋል። በፈቃድ ሥነ ሥርዓቱ ወቅት፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች ኢንቨስተሮች በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ላይእንዲደርሱ በማድረግ፣ በካፒታል ገበያ ልማት እና በኢንቨስተሮችጥበቃ ረገድ ያላቸውን ወሳኝ ሚና አፅንዖት ሰጥተዋል። በተጨማሪም ዋና ዳይሬክተሯ ፈቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ለኢንቨስተሮች ጥቅም ቅድሚያ እንዲሰጡ፣ ግልጸኝነትን እንዲጠብቁ እና ለካፒታል ገበያ የቁጥጥር ማዕቀፎች ተገዥነትን እንዲያረጋግጡ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ቢ ዲ ኦ ኮንሰልቲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበርን እንኳን ደስ አላችሁ በማለት በኢትዮጵያ ዘላቂየኢኮኖሚ እድገትን እና የኢንቨስተሮችን ጥበቃ የሚደግፍጠንካራ እና አካታች የካፒታል ገበያ ለማጎልበት ያለውንቁርጠኝነት በድጋሚ ይገልጻል።

---

**ለጥያቄዎችና ተጨማሪ መረጃ**
**የኮሙኒኬሽን እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት**
**ስልክ:** 011-5-57-81-62
**ኢሜይል:** communication@ecma.gov.et